# 3. የባህል አፈንጋጭነት ግንዛቤና መንስኤዎች በተማሪዎች፣ በመምህራንና በሃይማኖት አባቶች እይታ ፡ - በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ተተኳሪነት

ምንታምር ልንገርህ[1]፣ አለማየሁ ተመስገን[2]፣ ካሳሁን ደስያለው[3]

## አጽኅሮተ ፅሑፍ

ይህ ጥናት የተካሄደው “የባህል አፈንጋጭነት ግንዛቤና መንስኤዎች በተማሪዎች፣ በመምህራንና በሃይማኖት አባቶች እይታ ፡ - በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ ነው፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን ለማጥናት ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤና የፍንገጣ መንስኤዎች በሳይንሳዊ መንገድ ማጥናትና ወደ አካዳሚያዊ ውይይት ማምጣት ሲሆን ሌላኛው አነሳሽ ምክንያት በተለያዩ ድህረ ገፆችና ቤተ መፃሕፍት ባካሄድነው ዳሰሳ በዚህ ማህበረሰብ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተጠና ጥናት ባለማግኘታችን ይህንን ክፍተት ለማጥበብ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም ተማሪዎች፣ መምህራንና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤና የፍንገጣ መንስኤዎች መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥምር የምርምር ዘዴን በመከተል በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ እድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ሶስት ወረዳዎች (ስናን፣ ጎዛምንና እነማይ) ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ከሚገኙት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች/እናቶችን በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠው መረጃዎች ቀዳማይና ካዕላይ የመረጃ ምንጮችን በመጥቀም በቃለመጠይቅ፣ ጹሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት አሃዛዊና አይነታዊ መረጃዎችም በመቶኛ፣ በቀላል የልይይት ትንተና (One-Way ANOVA) እና የይዘታቸውን ተመሳሳይነት በመጠቀምና በምድብ በመከፋፈል ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለባህል አፈንጋጭነት

---

[1]ረ/ፕሮፌሰር ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ፎክሎር መምህርት፣ ስልክቁጥር 0910042426፣ E-mail: lmintamir@gmail.com

[2]ፒኤችዲ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል አማረኛ የማስተማር ስነዘዴ መምህር

[3] ረ/ፕሮፌሰር ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ ሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል የሶሾሎጅ መምህር

ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ተመሳሳይና ዝቅተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሰዎች ይዘውት ከነበረው ባህል የሚያፈነግጡበት መንስኤ በአስተዳደግ፣ በአቻ ግፊት፣ የነበረውን ባህል ጎጅ ሆኖ ሲያገኙት፣ በማህበራዊ ሚዲያና በመገናኛ ብዙሀን ተፅዕኖ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ የጥናቱን ግኝት መሰረት በማድረግም ለባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ለመገናኛ ብዙሀን፣ ለቀጣይ ተመራማሪዎች እና ለወላጆች የይሁንታ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት**: የባህል አፈንጋጭ፣ የፍንገጣ መንስኤ

# 1.መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

### 1.1.1 የፍንገጣ ምንነት

ስለፍንገጣ/አፈንጋጭነት ምንነት የተለያዩ የማህበረሰብ ሳይንስ ሙሁራን የየራሳቸውን ብያኔ አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Irani(2008) (David፣2000)ን በመጥቀስ ፍንገጣ ማለት አሁን እየቀጠለ ካለው ማህበራዊ ስርዓት (social pattern) ውጭ እንግዳ የሆነ ማህበራዊ ፀባይ መልመድ ነው ሲሉ በይነውታል፡፡ Irani(2008) አያይዘውም (Edgerton፣ 1976)ን በመጥቀስ ማህበራዊ ቁጥጥሩ ፍፁም የሆነበት ሥርዓት የለም፤ ምንም እንኳ ለማህበረሰቡ ባህል ግብ አለመሆን (non-confirmity) ማህበራዊ ፍንገጣ ተደርጎ ቢታሰብም የተወሰኑ ግለሰቦች በታወቀው የማህበረሰብ ባህል ውስጥ እንደሚጠበቁት ሆነው ላይገኙ ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

Long (2012) በበኩላቸው Goode (1997፣37)ን በመጥቀስ ፍንገጣ አንፃራዊ ትርጉም አለው ይላሉ፡፡ ይህን በምሳሌ ሲያስረዱ Nelson Mandela ለአመታት ያህል በደቡብ አፍሪካ ለገዥው ፓርቲ አደገኛ የፖለቲካ አፈንጋጭ ተደርጎ ይታይ ነበር፤ ነገር ግን ለብዙኂኑ ጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን የነፃነት ንቅናቄው የተከበረ መሪ ተደርጓል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ታዋቂው ሶሾሎጂስት ኢሚል ዱርካይም ደግሞ አፈንጋጭነት ሰዎች በቡድን እስከ ኖሩ ድረስ ሊፈጠር የሚችል ማህበራዊ እውነት ሲሆን ከነባራዊው ባህል ወጥቶ ማፈንገጥ በጣም አስፈላጊ ነገር ሊሆን እንደሚችል ተንትኗል፡፡ ይህን ሀሳበ አያይዞም Salinger (1998)

አፈንጋጭነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሞራል ወሰን በማስቀመጥ ተቀባይነት ባለው እና በሌለው የሰዎች ባህርይ መካከል ድንበር ለማበጀት ይረዳል ይላል፡፡

ባጠቃላይ ፍንገጣ ማለት ከነባራዊው ማህበራዊ ደንብ መውጣት፣ ማህበራዊ ለውጥ እንዲመጣ መፈለግ፣ ከለውጥ ጋር ራስን ማስተካከል፣ የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች የራሳቸውን አጀንዳ ለቀሪው የማህበረሰብ ክፍል ማስተዋወቅና የራሳቸውን ክብር በመጠበቅ አዲስ ባህልን በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ለማስረጽ መሞከር ነው፡፡

### 1.1.2 የፍንገጣ ዓይነቶች

Irani (2008) "*የማህበራዊ ፍንገጣ መንስዔዎችን መፈለግ*" (Exploring Causes of Social Deviation) በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ሶስት ዓይነት ፍንገጣዎች አሉ ይላል፡፡ እነሱም፡-

1ኛ. **ተቀባይነትን ያላገኘ** (disapproved) **ፍንገጣ፡-** ይህ የፍንገጣ ዓይነት የተወሰኑ ሰዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የማህበረሰቡን ህግ ወይም ሥርዓት የሚጥሱበት ሁኔታ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ወንጀለኞችን (criminals)ና ቀማኞችን (robbers) ማንሳት ይቻላል በማለት ይገልፃሉ፡፡

2ኛ. **ተቀባይነትን ያገኘ (approved) ፍንገጣ፡-** ይህ የፍንገጣ ዓይነት ደግሞ የተወሰኑ ግለሰቦች ለማህበረሰቡ አይጠቅምም ብለው ያሰቡትን ህግና ደንብ መብታቸውን ተጠቅመው በመጣስ አፈንጋጭነታቸውን በቃልና በድርጊት የሚገልፁበት ሁኔታ ነው፡፡ ራሳቸውን ከሌሎች አይደብቁም፡ ፡ እንዲያውም ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲከተሏቸው ያበረታቷቸዋል፡፡ እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች አቢዮተኛ ይባላሉ፤ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድም ተቀባይነትን ያገኙ ናቸው፡፡

3ኛ. **አንፃራዊ እና ፍፁም ፍንገጣ (Relative and Absolute deviation):-** በዘመናዊ ማህበረሰብ ውስጥ አብዛኛው ህዝብ ፍፁም አፈንጋጭ ወይም ፍፁም ተቀባይ አይደለም፡፡ ፍፁም አፈንጋጭ ሰው በህይወት ለመኖር አስቸጋሪ ይሆንበታል:: (wallerstein & wyle ,1974, Gold, 1970)ን በመጥቀስ እንዳቀረበው "ጤነኛ ሰው" ሁሉ በተወሰነ ደረጃ ያፈነግጣል ይላል፡፡

### 1.1.3 የባህል ፍንገጣ መንስዔዎች (causes of cultural deviation)

ከባህል የማፈንገጫ መንስኤዎች በተመለከተ Irani (sep. 23፣2008) እንዲህ ሲሉ በዝርዝር አስፍረዋቸዋል፡፡

1ኛ. **የቤተሰብ ቁጥጥር ማነስ** (lack of socialization) ፡- ቤተሰብ ለልጆች ጥሩ እና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህን አለማድረግ ግን ለፍንገጣ ያጋልጣል፡፡

2ኛ. **ግትርነት** (Ridged): - የማህበረሰቡ ባህል ግትር (not-flexible) እና ከለውጥ ጋር የማይጓዝ (un-compatible) መሆን ለፍንገጣ መንስኤ ይሆናል፡፡

3ኛ. **ተቀባይነት የሌለው ማህበራዊ ህግ** (unpopular social laws) ፡- መንግስት ህግ ሲያወጣ ከራሱ እንጅ ከህብረተሰቡ ፍላጎት አንፃር ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ዜጎች ሊያፈነግጡ ይችላሉ፡፡

4ኛ. **የባህል ወረራ** (cultural invasion) ፡- በከፍተኛ ሁኔታ ሰዎች በሌላ ባህል ሲጋለጡ ከራሳቸው ባህል ያፈነግጡና የሌሎችን ባህል ይለምዳሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የቤተሰብ ቁጥጥር ማነስ፣ የባህል ግትርነት፣ ተቀባይነት የሌለው ማህበራዊ ህግ እንዲሁም የባህል ወረራ ለፍንገጣ ዋና ዋና መንስኤዎች መሆናቸውን ነው፡፡

### 1.2.የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማካሄድ ስንነሳ ባካሄድን ነው የተለያዩ ቤተመፅሀፍት እና ድህረ ገፅ ዳሰሳ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ጥናት በስፋት አላገኘንም፡፡ ነገር ግን በተወሰነ መልኩ ግንኙነት ያለው Jaonan Cheng “The Effect Factor for Students’ Deviant Behavior” በሚል ርዕስ በ2012 ያካሄደው ጥናት የተማሪዎች የአፈንጋጭነት ባህርይ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዳለ ገልፆ ለተማሪዎች አፈንጋጭነት ጉልህ ድርሻ የሚጫወተው ከወላጆች ይልቅ የአስተማሪዎች ተጽዕኖ እንደሆነ ባካሄደው ስታስቲካዊ ፍተሻ አሳይቷል፡፡ Hossain የተባለ ሙሁር ደግሞ “Deviant Behavior: A Study of Causes” በሚል ርዕስ በ2014 ባጠናው ጥናት የአፈንጋጭነት ምክንያቶች በጣም በርካታ እንደሆኑ ገልጾ እነዚህም የራሳቸው የሆኑ ውስጣዊና ውጫዊ መሰረቶች እንዳሏቸው አብራርቷል፡፡ እነዚህ ምክንያቶችም በጊዜ፣ በቦታና በተለያዩ ሁኔታዎች ሊለያዩ እንደሚችሉ በጥልቀት አስረድቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰላም የተባለች ተመራማሪ “The School and Deviant Behavior: A Case Study of Youth in Bole Secondary High School and Dandi Boru School in Addis Ababa” በሚል ርዕስ በ2011 ባጠናችው ጥናት በተማሪዎች ዘንድ የሚታዩ የአፈንጋጭነት ዓይነቶች፣ የችግሩ ግዝፈት እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች

አፈንጋጭነት ያለውን አስተዋጽኦ ለመዳሰስ ሞክራለች። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በተማሪዎች ዘንድ በአደገኛነት የሚንፀባረቀው የአፈንጋጭነት ባህርይ አደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነት፣ አልኮል መጠጣት፣ ጫት መቃም፣ ሽሻ ማጨስ፣ ሲጋራ ማጨስ እንዲሁም ያለጊዜው የግብረ ስጋግንኙነት በስፋት መተግበር ናቸው።

በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ፣ Alemayehu “Assessment of Students Misbehavior and Coping Strategies: In the Case of Shashemene Secondary School” በሚል ርዕስ በ2012 ባጠናው ጥናት መሰረት በተማሪዎች ላይ የሚታየው የስነ-ምግባር ብልሽት እና አፈንጋጭነት በጣም አሳሳቢ ደርጃ ላይ እንደደረሰ ገልጾ ከአራት ተማሪዎች በአንደኛው ላይ እንደዚህ አይነት ችግር እንደሚንጸባረቅ አስቀምጧል። የአፈንጋጭነት ችግር በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይም ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ እንዳለ በጥናቱ ውጤት አመልክቷል። ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱ የጥናት ውጤቶች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከዚህ ጥናት መሰረታዊ አላማ ጋር የሚገናኝ ቢመስልም ሰፊ የሆነ ልዩነት እና የጥናት ክፍተት (Research Gap) እንዳለ እንረዳለን። ለምሳሌ ያህን ከላይ የተጠቀሱ ጥናቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ግንዛቤ እና በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ስላለው የመገንዘብ ልዩነት አንዳቸውም አልዳሰሱም። ከዚህ በተጨማሪ እነኚህ ጥናቶች የተሰሩበት የማህበረሰብ ክፍል ወይም ደግሞ ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ ከዚህ ጥናት ጋር የሚገናኝ ስላልሆነ እንደአንድ የጥናት አነሳሽ ክፍተት (Research Gap) ሊወሰድ ችሏል።

ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለአፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ከነዚህም መካከል በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚኖሩ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች መካከል ስለአፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤና ልዩነት ማመልከት፣ መምህራን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ከባህላቸው ለምን እንደሚያፈነግጡ መግለፅ እንዲሁም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስአፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መግለፅ ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤና የፍንገጣ መንስኤዎች መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1ኛ. መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለአፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት፣

2ኛ. በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል አፈንጋጭነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር፡

3ኛ. መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ከባህላቸው የሚያፈነግጡበትን መንስኤ መግለፅ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዋና አበርክቶ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1ኛ. መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለአፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ይጠቁማል፡፡

2ኛ. በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከለ ስለባህል አፈንጋጭነት የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

3ኛ. ወደ ፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

4ኛ. በባህል አፈንጋጭነት ዙሪያ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለማቀድ እና ለመስጠት ትልቅ ግብዓት ይሆናል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በምስራቅ ጎጃም ዞን በሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ቢሆንም ከጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ አንፃር በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ከተማሪዎች አንፃርም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ጥናቱ አያካትትም፡፡ ምክንያቱም በዚህ የእድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ያላቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸው አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ዝቅተኛ ስለሆነ ስለአፈንጋጭነት ያላቸው ግንዛቤ በአንፃራዊነት አነስተኛ ነው ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡ ሌላው መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየት የሚሞከረው ለአብነት የሚሆኑ የተወሰኑ ጭብጦችን ማለትም የተለያዩ ምሁራን ስለባህል

አፈንጋጭነት ምንነት ያቀረቧቸውን የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችንና በማህበረሰቡ የእለት ከእለት ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው የታሰቡትን የተወሰኑ ድርጊቶችን ብቻ በማቅረብ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸውን ግንዛቤ ፈትሿል እንጂ ሁሉንም ድርጊቶች አልተመለከተም፡፡

ሌላኛው የጥናቱ ወሰን ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም የዚህ ጥናት ዋና ርዕሰ ጉዳይ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር የሚል ነው፡፡ ምንም እንኳን በጥናት የተረጋገጠ እውነታ ባይሆንም በእለት ከእለት ህይወታችን እንደምንሰማው ባህላችን ተበረዘ፣ ተጣሰ፣ ተለወጠ ከሚሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የሃይማኖት አባቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ መምህራንና ተማሪዎች ደግሞ አዲስ አስተሳሰብ፣ ለውጥ አራማጅ (ምናልባትም አፈንጋጭ) ተደርገው ይታያሉ፡፡ እናም እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለአፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ የተለያየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ይመስላሉ፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት በተጨባጭ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየትና በመካከላቸውም ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ጥናቱ በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡

### 1.6. የቃላት ሙያዊ ብያኔ

**ፍንገጣ/አፈንጋጭነት፡-** በዚህ ጥናት ፍንገጣ/አፈንጋጭነት ማለት ማህበረሰቡ ከሚከተለው ደንብ መውጣት ማለት ነው፡፡

**የፍንገጣ ግንዛቤ፡-** በዚህ ጥናት የፍንገጣ ግንዛቤ ሲባል የፍንገጣ ምንነትን፣ ዓይነቶችን፣ መንስኤዎችን፣ ባህርያትን እና በባህል ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

## 2. የአጠናን ንድፍና ዘዴ

### 2.1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱን ፍልስፍናዊ አነሳስ ስንመለከት ይህ ምርምር በፕራግማቲዝም አተያይ (pragmatic worldview) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በፕራግማቲዝም ፍፁም የሚባል እውነት የለም፤ እውነት የሚባለው አሁን ያለው ነው፤ እውነት በሂደት የሚሻሻል ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ እውነታ ወይም ፍልስፍና ላይ የተወሰነ አይደለም፡፡ ፕራግማቲዝም ተመራማሪው በችግሩ ምንነትና

እንዴትነት ላይ በማተኮር የፈለገውን ሥነ ዘዴ፣ ስልት እና አካሄድ እንዲጠቀም ይፈቅዳል፡፡ በሌላ አባባል ይህ አተያይ ለጥምር የምርምር ዘዴ (mixed research method) የፍልስፍና ማዕቀፍ የሚሰጥ ነው (Creswell, 2009, 10-11; Muijs, 2004,7)፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት በዋናነት ገላጭ ቅኝታዊ ንድፍን (descriptive survey) የተከተለ ሲሆን ከምርምር ዘዴ አንፃር ደግሞ በአሃዛዊ ዘዴ (quantitative method) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዓይነታዊ ዘዴንም ተግባራዊ የሚያደርግ ነው፡፡ ባጭሩ ቅይጥ ዘዴን (mixed research method) የተከተለ ነው ማለት ይቻላል (Creswell,2009)፡፡ በቅይጥ ዘዴ ውስጥ እንደገና ዓይነታዊ እና አሀዛዊ መረጃዎች ትይዩ በሆነ መንገድ የሚተነተኑበትን ሁኔታ የሚያመለክት በመሆኑ ጎናዊ ቅይጥ ዘዴን (concurrent mixed research method) የተከተለ ነው፡፡

## 2.2. የምርምሩ ስነ-ዘዴ

### 2.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት እድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም በምስራቅ ጎጃም ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ሶስት ወረዳዎች ተመርጠዋል፡፡ ይህን የንሞና ዓይነት መጠቀም ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ለሁሉም ወረዳዎች እኩል እድል ለመስጠትና በመጨረሻም የሚገኘውን ውጤት ለሁሉም ወረዳዎች ለማጠቃለል ሲባል ነው፡፡ በመቀጠል በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች እንደሚከተለው ተመርጠዋል፡፡

### 2.2.2. የተጠኝዎች አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለአፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ነው፡፡ ይሁን እንጅ ጥናቱ ከገንዘብ፣ ከጊዜ እና ከጉልበት ወጭ አንፃር ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ማካተት ስለማይችል በምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ከሚገኙ ወረዳዎች (ስናን፣ጎዛምንና እነማይ) ውስጥ የሚገኙ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተሳታፊ ሁነዋል፡፡ ጥናቱ በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ በዋናነት ያተኮረበት ምክንያት እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት የተለያየ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

Cohen (2000፣95) እና Zoltan (2010፣63) ትክክለኛ የናሙና መጠን ምን ያህል ነው የሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ የለውም ምክንያቱም እንደ ጥናቱ ዓይነት፣ እንደ ጥናቱ ዓላማ እና እንደ አካላዩ ባህሪ ይወሰናል በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በጥናቱ እንዲሳተፉ የፅሁፍ መጠይቅ የተሰጣቸው መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ብዛት አንድ መቶ ሃያ (120) የነበረ ቢሆንም መረጃውን አሟልተው ያልመለሱ 23 ተጠኝዎች በመኖራቸው የተነሳ ቁጥራቸው ወደ 97 ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከ3ቱ ወረዳዎች ውስጥ በጥናቱ የተሳተፉ 32 መምህራን፣ 34 ተማሪዎችና 31 የሃይማኖት አባቶች በጠቅላላው 97 ተጠኝዎችን ለመምረጥ የምድብ ንሞና ዘዴ (quota sampling method) ተግባራዊ ሁኗል፡፡ ምክንያቱም ምድብ የናሙና ዘዴን የምንጠቀመው "የጥናቱ አካላይ በጣም ብዙ የሆኑ አባላት ሲኖሩትና ዝርዝራቸውን ማግኘት አልያም ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ነው" (ያለው እንዳወቀ፣ 2001፣133)፡፡

### 2.2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሑፍ መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም እንዴትና ምን ዓይነት መረጃ እንደተሰበሰበ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

#### 2.2.3.1. የፅሁፍ መጠይቅ

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ዝግና ክፍት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለተሳታፊዎች ቀርበዋል፡፡ ዝግ ጥያቄዎች በሊከርት ወይም በሬቲንግ ስኬል መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት በክፍል አንድ የተጠኝዎች አጠቃላይ መረጃ ማለትም ዕድሜ፣ ጾታ፣ የስራ ዓይነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ የቀረቡበት ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አዎንታዊና አሉታዊ ጥያቄዎች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻም በክፍል ሶስት ተጠኝዎች ስለባህል አፈንጋጭነት ግንዛቤና መንስኤ በሚመለከት ክፍት ጥያቄዎች ተለይተው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

#### 2.2.3.2. ቃለ መጠይቅ (Interview)

ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን በመጠቀም በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱ ሶስት ወረዳዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት

አባቶች ስለአፈንጋጭነት ግንዛቤና መንስኤ በተመለከተ የጥናቱን ዓላማዎች ታሳቢ በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋ። ይህን የተደረገው በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ይበልጥ የተሟሉ እና ገላጭ እንዲሆኑ ታስቦ ነው።

### 2.2.3.3. ቡድን ተኮር ውይይት

በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለአፈንጋጭነት ግንዛቤና መንስኤ በተመለከተ ከላይ በፅሁፍ መጠይቅ የቀረቡትን ዓላማዎች ታሳቢ በማድረግ ለተወሰኑ ተጠኝዎች ማለትም በጥናቱ ውስጥ በተካተቱ ሶስት ወረዳዎች ከሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ቡድን ተኮር ውይይት በድምሩ 30 ተጠኝዎችን (2*5*3) በአመቺ የንሞና ዘዴ በመምረጥ እና ክፍት ጥያቄዎችን በቃለ መጠይቅ መልክ በማቅረብ ተጨማሪ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዘዴ ነው፡፡ ከሌሎች ዘዴዎች ይልቅ ቡድን-ተኮር ውይይት የተመረጠበት ምክንያት Cohen,et al. (2000፡ 288) እንደሚሉት የቡድን ውይይት ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች አንፃር ሲታይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ከመሆኑ ባሻገር የተለያዩና እርስ በእርስ የሚቃረኑ ሀሳቦች በሚወጡበት ጊዜ ሰፉ ያለ ክርክር ለማድረግና ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 2.2.3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት

የፅሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል በመስኩ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች መጠይቁን እንዲያዩትና ሃሳብና አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ በመጠይቁ ላይ ጭማሪ፣ ማሻሻያ እንዲሁም የተወሰኑ ጥያቄዎች እንዲቀሩ ተደርጓል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለማወቅ ደግሞ በ'ክሮንባክአልፋ' ተሰልቶ ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ የሚመልሱ ዓረፍተ ነገሮች 0.63 አልፋ ውጤት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 2.3. የመረጃ መተንተኛ ስልቶች

በዚህ ጥናት አሃዛዊና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ይኸውም ለፅሁፍ መጠይቆች ተጠኝዎች የባህል አፈንጋጭነት ምንነትን አስመልክቶ በሊከርት ስኬል ለቀረቡላቸው ዐረፍተ ነገሮች የሰጧቸውን ምላሾች ወደ አሃዝ በመለወጥ ከዓይነተኛ ገላጭ ልኬታዎች መካከል አማካይ ውጤትን (Mean Score) እና መደበኛ ልይይትን (Standard

Deviation) በመጠቀም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ ወደ ሦስት (ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ) ተከፍሏል። የእነዚህን ደረጃዎች የመቁረጫ ነጥብ (Cut off Point) ለማወቅ የተገኙትን የመደበኛ ልይይት ውጤቶች ግማሽ (Half Standard Deviation) ከአማካይ ውጤቶች ላይ በመቀነስ እና በመደመር (ወይም 1/2 መደበኛ ልይይት± አማካይ ውጤት) የሚለው ቀመር ጥቅም ላይ ውሏል (Field, 2009) ።

በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ደግሞ ቀላል የልይይት ትንተና ዘዴ (One-Way ANOVA) በ0.05 የስህተት ይሁንታ መጠን (α) አገልግሎት ላይ ውሏል። የትንተና ውጤት በሦስቱ ቡድኖች መካከል የግንዛቤ ልዩነት መኖሩን ባሳየ ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን ከሌላኛው ቡድን መብለጡን ወይም ማነሱን ለማወቅ የቦንፌሮኒ ድህረ ንጽጽር ፍተሻ (Bonferroni Post-hock Comparison Test) ተግባራዊ ሆኗል (Field, 2009) ።

ከክፍት የፅሁፍ መጠይቅ እና ከቡድን- ተኮር ውይይት የተገኙትን አይነታዊ መረጃዎች ደግሞ የይዘታቸውን ተመሳሳይነት በመጠቀምና በምድብ በመከፋፈል ተተንትነው በእያንዳንዱ አሃዛዊ መረጃ ትንተና ውጤት ስር ቀርበዋል።

## 2.4. ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ለምርምሩ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በነፃነት መስጠት እንዲችሉ የምርምር ሥነ-ምግባር መከበር አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የትብብር ደብዳቤ ከማፃፍ ጀምሮ ከመረጃ ሰጭ አካላት (ከሃይማኖት አባቶች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች) ጋር ስለምርምሩ ምንነትና ዓላማ ውይይት በማድረግ በምርምር ስራው በቅንነት እንዲሳተፉና መረጃ የመስጠት ሂደቱ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል። በዚህ ጊዜ ለምርምሩ የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ እንደማይውልና የመረጃ ሰጭዎች ማንነትም ለማንም እንደማይገለፅ ተነግሯቸዋል። ባጠቃላይ የአሜሪካ የሥነ-ልቦና ማህበር በ2017 ያወጣው የምርምር ሥነ-ምግባር በስራ ላይ ውሏል።

## 3. የመረጃ ውጤት እና ትንተና

በጥናቱ ዓላማ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሄደበት ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤና የፍንገጣ መንስኤ መመርመር ሲሆን ይህን ዋና ዓላማ ለመመለስ ደግሞ መረጃዎች ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች በፅሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስበው በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች ዳራዊ መረጃ

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ የጥናቱ ተሳታፊዎችን የተለያዩ ዳራዊ መረጃዎች፣ ማለትም ጾታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሚኖሩበት አካባቢ እና የእድሜ ሁኔታቸውን የሚያሳይ አሃዝ ተጠናቅሮ ተቀምጧል፡፡

ሰንጠረዥ 3.1 ዳራዊ መረጃ

| ተላውጦዎች | | የተሳታፊዎች ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሀይማኖት አባት/እናት | | መምህራን | | ተማሪዎች | |
| ፆታ | ወንድ | 30 | 96.8% | 16 | 50.0% | 18 | 52.9% |
| | ሴት | 1 | 3.2% | 16 | 50.0% | 16 | 47.1% |
| የትምህርት ደረጃ | ድግሪ | 2 | 6.5% | 11 | 34.4% | 0 | 0.0% |
| | ዲፕሎማ | 2 | 6.5% | 4 | 12.5% | 0 | 0.0% |
| | ዲያቆን | 10 | 32.3% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |
| | 2ኛ ደረጃ ትምህርት | 2 | 6.5% | 13 | 40.6% | 34 | 100.0% |
| | ቄስ | 11 | 35.5% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |
| | ሁለተኛ ድግሪ | 0 | 0.0% | 4 | 12.5% | 0 | 0.0% |
| | መሪጌታ | 4 | 12.9% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |
| ከተማ | እነማይ | 9 | 29.0% | 8 | 25.0% | 0 | 0.0% |
| | ጎዛምን | 20 | 64.5% | 13 | 40.6% | 22 | 64.7% |
| | ስናን | 2 | 6.5% | 11 | 34.4% | 12 | 35.3% |
| እድሜ | ብዛት (n) | 31 | | 32 | | 34 | |
| | ዝቅተኛ | 19 | | 26 | | 16 | |
| | ከፍተኛ | 69 | | 56 | | 21 | |
| | አማካይ | 36.58 | | 33.91 | | 18.59 | |
| | መደበኛ ልይይት | 12.31 | | 5.99 | | 1.351 | |

ከሰንጠረዥ- 3.1 እንደምንመለከተው ለዚህ ጥናት ዓላማ መሳካት ሲባል መረጃ የሰጡን የህብረተሰብ ክፍሎች 31 የሀይማኖት አባቶች /እናቶች፣ 32 መምህራን እና 34 ተማሪዎች

ናቸው፡፡ ከፆታ አንፃር ከሀይማኖት አባቶች/ እናቶች በስተቀር መምህራንና ተማሪዎች በቁጥር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ ከትምህርት ደረጃ አንፃር ከ31 የሀይማኖት አባቶች/እናቶች ውስጥ 2 በድግሪ፣ 2 በዲፕሎማ፣ 10 በዲቁና፣ 2 በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ 11 በቅስና እና 4 በመሪጌትነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ መምህራንን በተመለከተ ደግሞ 11 የመጀመሪያ ድግሪ፣ 4 ዲፕሎማ፣ 13 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ፣ 4 ሁለተኛ ድግሪ ያላቸው ሲሆኑ ተማሪዎች ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከቦታ አንፃር ሶስቱም የህብረተሰብ ክፍሎች የተመረጡት ከሶስት ወረዳዎች ሲሆን እነዚህም ጎዛምን፣ ስናንና እነማይ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የተጠኝዎችን እድሜ በተመለከተ ከ16 እስከ 69 የእድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆን በተለይም ተማሪዎችን በተመለከተ ከእድሜ አንፃር ሊፈጠር የሚችለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር ሁሉም ተማሪዎች 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## 3.2. መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለአፈንጋጭነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ

ሰንጠረዥ - 3.2 መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ

| የተሳታፊዎች ምድብ | ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| የሃይማኖት አባቶች/እናቶች | 23 (74.2%) | 8 (25.8%) | 0 (0.0%) |
| መምህራን | 19 (59.4%) | 12 (37.5%) | 1 (3.1%) |
| ተማሪዎች | 23 (67.6%) | 11 (32.4%) | 0 (0.0%) |

ከላይ ከቀረበው ከሰንጠረዥ- 3.2 እንደምንመለከተው የሃይማኖት አባቶች/እናቶች፣መምህራንና ተማሪዎች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ለ31 የሃይማኖት አባቶች የፅሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 23(74.2%) ያህሉ በዝቅተኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆኑ 8(25.8%) የሚሆኑት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው፡፡ በከፍተኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው የሃይማኖት አባቶች ግን የሉም፡፡ የፅሁፍ መጠይቅ ከቀረበላቸው 32 መምህራን መካከል 19 (59.4%) ያህሉ በዝቅተኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆኑ 12 (37.5%) የሚሆኑት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው፡፡ 1 (3.1%) መምህር ብቻ ከፍተኛ ግንዛቤ ያለው ሁነው ተገኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል 34 ለሚሆኑ ተማሪዎች ከቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው 23 (67.6%) ያህሉ በዝቅተኛ ደረጃ ግንዛቤ ያላቸው

ሲሆኑ 11 (32.4%) ያህሉ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የሉም። ከዚህም የሃይማኖት አባቶች/እናቶች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ስለአፈንጋጭነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ተመሳሳይና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ ባሻገር በመካከላቸው የተወሰነ ልዩነት ቢኖር እንኳ ይህ ልዩነት ጉልህ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ቀላል የልይይት ትንተና (one-way ANOVA) በመጠቀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ከመጠናዊ የመረጃ መሰብሰበያ እና መተንተኛ ዘዴዎች በተሻለ ሁኔታ የአይነታዊ ዘዴዎች በተሻለ ጥልቀት እውነታው ሊደርስሱበት እና ሊገልፅ እንደሚችል የጥናት ዘዴዎች ንጽጽር መጽሀፍት ያስረዳሉ። ከዚህ በመነሳት ስለአፈንጋጭነት የአይነታዊ ዘዴዎች በቂ መረጃ ተሰብስቧል። በመሆኑም ስለአፈንጋጭነት ምንነት እና ከባህል ለማፈንገጥ መንስኤ የሚሆነው መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ተተንትነዋል።

ከሃይማኖት አባቶች ጋር የተደረገው ውይይት ልክ ከላይ በመጠናዊ/ስታስቲካዊ መንገድ በሰንጠረዥ እንደተገለጠው ሁሉ ስለባህል አፈንጋጭነት የተሟላ ያልሆነና ወደ አንድ ጎን ያጋደለ ግንዛቤ እንዳለ መረዳት ይቻላል። ይህንን በተመለከተ የ66 አመት የእድሜ ባለጠጋ የሃይማኖት አባት የሰጡንን ሀሳብ ቃል በቃል እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡-

> *…ባጭር አማርኛ ለማስቀመጥ ከባህል ማፈንገጥ ማለት ካባቶቻችን የወረስነውን ወግ እና ባህል ወደጎን በመተው የባዕድ የሆነን አኗኗር መከተል ማለት ነው። የዚህ ደሞ መሰረቱ እናት እና አባትን ካለመስማት እና ካለማክበር የሚመጣ ነው። እኛ እኮ ድሮ ስናድግ እንኳን ልናፈነግጥ ቀርቶ ቀና ብለን አናይም ነበር፣ ትልቅ ሰው በመንገድ ሲያልፍ እንኳን ቀና ብለን አናይም ነበር። የአሁን ዘመን ልጅ እንዲያ ሁን ብትለው እናጃልህ ነው የሚልህ ማን ይሰማሃል። ሚስቱንም ሆነ ባሉን እዛው በሜዳ ነው ጨርሶ የሚመጣ እና ካለቀ በኋላ ና ውል ያዝ የሚባል፣ ብልግናው ትል፣ የሴቱ አለባበስ ትል፣ ምኑ ቅጡ ማፈንገጥ የሚለው ራሱ ሲያንሰው ነው ጭራሽ መረን የለቀቀ ነገር ነው ማለት ይሻላል…"*

ከላይ የተቀመጠውን ስለባህል አፈንጋጭነት ከተሰጠ ሃሰብ የተሻለ በሚመስል መልኩ የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ ዲያቆን አፈንጋጭነትን ሁልጊዜ እንደነውር መቆጠር እንደሌለበት

እና አልፎ አልፎ ሁሉም ሰው በተወሰነ ደረጃ ከባህሉ ሊያፈነግጥ እንደሚችል በቡድን ውይይት ወቅት እንዲህ ሲሉ አስረድተዋል፡-

> *"...ከባህል ማፈንገጥ ማለት ባጭሩ የኛ መገለጫ የሆኑ ቱባ ባህሎቻችንን ወደ ጎን መተው ማለት ሲሆን ብዙ መገለጫዎች ሊኖሩት ይችላሉ። አንዳንዱ ቀለል ያሉ እና እንዲሁ ታዝበን የምናልፋቸው ነገሮች ሲሆኑ ብዙዎቻችን ባንድም በሌላ መንገድ ወጣ ማለታችን አይቀርም። ሌሎች ነገሮች ግን እጅግ አይን ያወጡ እና ጋጠወጥነት የሚባሉ ነገሮች አሉ እነዚህ ደግሞ እንደ ትልቅ ብልጋና የሚቆጠሩ እና ሊኮነኑ የሚገቡ ነገሮች ናቸው..."*

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ማፈንገጥ ሲባል ከባህላችን ተቃራኒ ነገር ማድረግ፣ ባህልን መሻር፣ መናቅ እና አለመተግበር ማለት እንደሆነ ደጋግመው አስረድተዋል። ሃሳባቸውን ለማጠናከር ሲሉም አክለው፣ *"...ሰዎች ዘመን አመጣሽ ነገር ለማድረግ ሲሉ ከባህላቸው አፈንግጠው ለሰውም ለራሳቸውም የማይበጃቸውን ነገር ይተገብራሉ ማለት ነው። የአያት የቅድመ አያታቸውን ውርስ እና ወግ ይሽራሉ..." ሲሉ አብራርተዋል።*

ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌሎች የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ መምህራን የባህል አፈንጋጭነት ከመጠናዊ ዘዴዎች የተሻለ በሚባል ደረጃ ገልጠውታል። ለአብነት ያህልም የ28 አመት እድሜ መምህር የባህል አፈንጋጭነትን በተመለከተ የሰጡንን ማስረጃ እንደሚከተለው መመልከት ይቻልለ፡- "...የባህል አፈንጋጭነት ማለት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በጋራ ተስማምተው ካወጧቸው ወይም ከአለፈው ትውልድ ከወረሷቸው ልማዶችና እሴቶች በመውጣትየሌላውን አካባቢ ባህል መከተል ነው። አሊያም ነባሩን ባህል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መተውና ማስቀረት ነው..."

ከዚህ በተጨማሪ የባህል አፈንጋጭነት መገለጫዎችን ዘርዘር አድረገው በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በአኗኗር ዘይቤ፣ በተለያዩ የበአላት ወይም የለቅሶ ክዋኔዎች፣ በአረማመድ፣ በአሰራር፣ በሰላምታ አሰጣት፣ በመገልገያ ቁሳቁሶች ሊገለጥ እንደሚችል አብራርተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሲወርድ ሲወራረድ የመጡ እና እንደልማድ የያዝናቸው ነገሮች ነገር ግን አላስፈላጊ እና ጎጂ የሆኑ አንዳንድ የባህል መገለጫዎች በራሳቸው ከባህል እንደማፈንገጥ ሊቆጠሩ እንደሚችሉ አንድ መምህርት እንደሚከተለው አስቀምጠዋል "…የባህል አፈንጋጭነት ማለት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን ባህል መቀየር ወይም መለወጥ ማለት ነው። ለምሳሌ፡- ለቅሶን ብንወስድ ለቅሶ ጠቃሚ ባህል ነው። ነገር ግን ደረት መምታት፣ ፊት መንጨት፣ ሱሪ በአንገት ይዞ መዞር ወዘተ እነዚህን ልምዶች መተው ከባህላችን ማፈንገጥ ወይም የአፈንጋጭነት ምልክት ነው…"

ከባህል አፈንጋጭነት ምንነት በተጨማሪ፣ አፈንጋጭነት ጠቃሚ ሊሆን የሚችልባቸዉ ሁኔታዎችን መረዳት ሌላኛዉ ስለአፈንጋጭነት ያለ የግንዛቤ ደረጃ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መምህራን አፈንጋጭነት ጠቃሚ ሊሆንባቸው የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ሲያብራሩ፤ "… አፈንጋጭነት የሚቆመው ለአወንታዊ ለውጥ ሲሆን፣ ጊዜን፣ ጉልበትንና ወጭን የሚቀንስ ከሆነ፣ ባህሉ አሉታዊ ተጽዕኖነቱ የሚያመዝን ከሆነ …" ሊሆን እንደሚችል ሚዛናዊ የሚባል ማብራሪያ አስቀምጠዋል።

ስለሆነም ጎጂ ከሆኑ ባህላዊ ልማዶች በምንወጣበት ጊዜ ማፈንገጥ ጠቃሚ ነው ሊባል እንደሚችል ከዚያም አልፎ ተርፎ ለሃገር እድገት ጠቃሚ ሁኖ ሲገኝ ማፈንገጥ ጠቃሚ ጎኑ እንደሚያመዝን አብራርተዋል።

ምንም እንኳን ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ቢሆኑም፣ በአይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ላይ ግን እንደሌሎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሰፋ ያለ ትንታኔ ሳያስቀምጡ ቀርተዋል። ሆኖም ግን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ አናሳም ቢሆን የአይነታዊ መረጃው የመጠናዊ መረጃውን በሚያጠናክር መልኩ እንደተገኘ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አፈንጋጭነትን ከብልግና/ወጣ ያለ ተግባር፣ ከተለመደው አኗኗር ወጣ በማለት ሰውን ማስቀየም፣ ልታይ ልታይ ማለት ወዘተ አይነት አገላለጾችን በመጠቀም ለመግለጽ እንደሞከሩ ጠቅለል አድርጎ ማቅረብ ይቻላል።

## 3.3. በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል አፈንጋጭነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት

ሰንጠረዥ 3.3 በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል አፈንጋጭነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት

| የልይይት ምንጭ | የካሬዎች ድምር(Sum of Squares) | የነፃነት ደረጃ (df) | አማካይ ካሬዎች (Mean Square) | F |
|---|---|---|---|---|
| በቡድኖች መካከል | 49.649 | 2 | 24.825 | .565* |
| በቡድኖች ውስጥ | 4000.957 | 91 | 43.967 | |
| ድምር | 4050.606 | 93 | | |

***p=.571** በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል አፈንጋጭነትን በተመለከተ ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ልዩነት የለም

ከላይ ከሰንጠረዥ 3.3 እንደምንመለከተው በ2 እና 91 የነፃነት ደረጃዎች፣ በ0.05 የጉልህነት ደረጃና በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ F= (2, 91, alpha=.571)=0.565 ነው፡፡ ይህ ውጤት ደግሞ ከተቀመጠው የp=.05 ዋጋ የበለጠ ነው፡፡ በመሆኑም በሶስቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት ስለሌለ ስለአፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ አማካይ ውጤታቸውን ማወዳደር አስፈላጊ አይደለም፡፡

ከሞላ ጎደል ስንመለከተው ስለ አፈንጋጭነት ያለው አይነታዊ መረጃ ከላይ የተቀመጠውን መጠናዊ ትንተና ሊያጠናክር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ስለአፈንጋጭነት ምንነት ያላቸው ግንዛቤ ስንመለከት ጠቅለል ባለመልኩ፣ ለየት ማለት በክፉም በደጉም፣ ወጣ ማለት፣ ቱባ ባህሎችን መተው፣ ስድ መሆን፣ መፈላሰፍ፣ ማህበረሰቡን የሚያስቀይም ነገር ማድረግ፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን ትውፊት መጣስ፣ የምራባዊያንን ባህል መከተል የሚሉ አገላለጾችን በብዛት እናገኛለን፡፡. ከዚህ በተጨማሪ የአፈንጋጭነት መገለጫዎችን ስንመለከት ሁሉም የጥናት ተሳታፊዎች በሚባል ደረጃ አፈንጋጭነት በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በጋብቻ፣ ከሃይማኖት ጋሪ በተገናኘ፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ እንዲሁም በዘር፣ በጾታ፣ በቀለም ከባህል ሊያፈነግጡ እንደሚችሉ አስቀምጠዋል፡፡

## 3.4. መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ከባህላቸው የሚያፈነግጡበት መንስኤ

ምንም እንኳን ስለአፈነጋጭነት ምንነት እና ተያያዥ ጉዳዮች መጠናዊ መረጃዎችም ሆኑ አይነታዊ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ ቢተነተኑም፣ ሰዎች ለምን ከባህላቸው ያፈነግጣሉ ለሚለው መሰረታዊ የጥናቱ አላማ ግን የአይነታዊ መረጃ ብቻ የተሰበሰበ ስለሆነ የሚከተለው ትንታኔም

እሱ ላይ ብቻ የተመሰረተ ይሆናል ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ከጉዳዩ ተለዋዋጭነት፣ ግለሰባዊነት እና ጥለቀት አንጻር መጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ትክክለኛውን እውነታ የማንጸባረቅ አቅም ላይኖራቸው ስለሚችል ነው። ስለሆነም የጥናቱ ተሳታፊዎች የራሳቸውን አመለካከት፣ ግንዛቤ እና አገላለጽ በመጠቀም ቢገለፅት የተሻለ ለእውነታው የመቅረብ እድል አለው ከሚል የአጥኚዎች ምክንያታዊ አስተሳሰብ ነው።

በመሆኑም ሰዎች ለምን ከባህላቸው ያፈነግጣሉ በሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ዙሪያ የተሰበሰቡት አይነታዊ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርቧል። በመረጃው መሰረትም ለባህል አፈንጋጭነት መንስኤ ናቸው ተብለው የተቀመጡ ነገሮች አንድ በአንድ በዝርዝር ተብራርተዋል።

i. ***አስተዳደግ፦****የተለያዩ የማህበረሰብ ሳይንስና ስነ-ባህርይ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚያረጋግጡት ከሆነ የሰዎች መሰረታዊ የባህርይ ስሪት የሚወሰነው በለጋ ልጅነት ወቅት ባሉ የአስተዳደግ ተጽኖዎች እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህም ነገር በጣም ጠንካራ እና ተጽዕኖው እስከ እድሜ ፍጻሜ ሊደርስ የሚችል ባህርይን የሚቀርጽ ሁኔታ እንደሆነም አክለው ያብራራሉ። አስተዳደግ ለአፈንጋጭነት ዋና መንስኤ ተደርጎ በጥናቱ ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ተገልጿል። ይህንን ሀሳብም አንድ የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ የሃይማኖት አባት በቡድን ውይይቱ ወቅት እንደሚከተለው አብራርተዋል፦ “አስተዳደጉ የተበላሸ ልጅ በተለይ እናት አባቱን ሳያከብር ያደገ ልጅ ምንም አይመልሰውም። ቢቆጡትም ቢቆነጥጡትም አይመለስም እና አስተዳደግ ወሳኝ ነገር ነው። …” አንድ ልጅ ሲያድግ የሚያድግበትን ማህበረሰብ ወግ ልማድ ጠብቆ ማደግ አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ያፈነገጠ ይሆናል።*

ii. ***የአቻ ግፊት፦*** *አፈንጋጭነትን በአመዛኙ ከወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ጋር በማያያዝ፣ የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ ዲያቆን የአቻ ግፊት ወጣቱን ከባህሉ እንዲያፈነግጥ ትልቅ ምክንያት እየሆነ እንደመጣ የታዘቡትን እንደሚከተለው አብራርተዋል፦*

> *“…አሁን በብዛት እንደምናየው ከሆነ አፈንጋጭነት በስፋት የሚታየው በአዲሱ ትውልድ ላይ ነው። በብዙ ነገር የራሳቸውን የለት ከእለት ፍላጎት እና እቅድ እንጅ የእናት አባታቸውን ትውፊት እና ወግ ብዙ ሲያስጨንቃቸው አይታይም። ከዚህ ተነስተን ለምን እንደሚያፈነግጡ ያየን እንደሆነ ዋናው ነገር የጓደኛ ግፊት ሊሆን ይችላል ብየ*

*አስባለሁ፡፡ ስለሆነም በትምህርት ቤትም ሆነ በጎረቤት የሚገናኙ ወጣቶች ቀስ በቀስ ወደ መጥፎ ተጽእኖ ውስጥ እየገቡ ሲበላሹ ይታያል፡፡ ሌላው ዋና ነገር ደግሞ በተለያዩ ሚዲያዎች የሚተላለፉ ነገሮች ያለምንም ገደብ ወደ ወጣቶች ጆሮ እና አይን ስለሚደርስ እና የተለያዩ ነውር የሆኑ ነገሮች በየቀኑ ስለሚተላለፉበት እሱ ከባድ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብየ አስባለሁ…”*

ከዚሁ ጋር አያይዘው የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ መሪጌታ ጠቅለል አድርገው የአፈንጋጭነት መንስኤዎችን አብራርተዋል፡፡ እንደሳቸው ሃሳብ ከሆነ ባብዛኛው ሰው ከባህሉ የሚያፈነጠው በተለያየ ምክንያት ነው፡፡ አንዳንዱ ተማርኩ፣ ሰለጠንኩ፣ ረቀቅሁ እያለ እንደሆነ፣ አንዳንዱ ደግሞ ባለማወቅ፣ የአስተዳደግ ችግር ያለበት እና ካገሩ በራቀ ቁጥር ባህሉንም እየረሳ እየተወ ይሄዳል ብለዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ወጣቱ ትውልድ ስንመለከት ከዚህ የዘለለ አይደለም ነገር ግን ቤተሰብ የሚለውን ምክር አለመስማት እና ከቤተ-ክርስትያን አስተምሮ እጅጉን መራቅ በራሱ ትልቅ ጠንቅ እንደሆነ እምነታቸውን አስረግጠው አብራርተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አሁን ስላለው አዲሱ ወጣት ትውልድ ሲናገሩ እሱ ካልመሰለው በስተቀር ምንም ነገር እማይቀበል ትውልድ እንደሆነና ይህም ነገር በቀላሉ ከባህላቸው እንዲያፈነግጡ እንደሚያደርጋቸው አብራርተዋል፡፡

iii. **የነበረው ባህል ጎጂ ሆኖ ሲያገኙት፡-** ሌላኛዉ ለአፈንጋጭነት እንደ ዋና ምክንያት ከተጠቀሱት ነገሮች መካከል ነባሩ ባህል በተለያየ መንገድ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ ሲመጣና ይህም ነገር በተለያዩ ሳይንሳዊ ግኝቶች እየተረጋገጠ ሲመጣ ሰዎች ለዚህ ባህል አሉታዊ አመለካከት እያሳደሩ ይመጡና ከጊዜ በኋላ ለማፈንገጥ ይገደዳሉ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ከነበረው ባህላቸው የተሻለ ወይም ለየት ያለ ነገር ሲያገኙ እና የነበረው ባህል ጎጅነቱ የሚያመዝን ከሆነ ከዚያ ለመራቅ ያፈነግጣሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመለከተ የ35 አመት እድሜ መምህርት ሰዎች ከባህላቸው የሚያፈነግጡበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ “…ባህሎች ሁሉ ጠቃሚ ሆነዉ በማይገኙበት ጊዜ ለምሳሌ ጎጂ ባህሎች የምንላቸዉ ያላቻ ጋብቻ፣የሴት ልጅ ግርዛት ወዘተ በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ማፈንገጥ ይቻላል…”

ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለጡት ብዙዎቻችን የምናፈነግጠው መጤ ባህልን መውደድ ወይም ዘመናዊነትን በራሳችን ባህል መፍጠር የሚቻል መሆኑን በመዘንጋት እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተው አብራርተዋል፡፡

iv. **የማህበራዊ ሚዲያና የመገናኛ ብዙሀን ተፅዕኖ፡-** የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ የሃይማኖት አባቶች እና መምህራን እንዳብራሩት ከሆነ ወጣቶች በየማህበራዊ ሚዲያውና በየመገናኛ ብዙሃኑ የሚመለከቷቸው ነገሮች ምን ያህል ከራሳቸው ባህል ወግና ስርዓት ጋር አብረው ይሄዳሉ ወይም አይሄዱም የሚለውን ሳያገናዝቡ ለመተግበር ይሞክራሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ከባህላቸው ያፈነግጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለራሳቸው ባህል ያላቸው ግንዛቤ የጠለቀ ባለመሆኑ በየሚዲያው በሚያዩት ነገር ይሳቡና የራሳቸውን ባህል እንደ ቀላል ነገር በማየት የውጭ ሃገራትን ልምድና ባህል በመቀላቀላቸው ሰዎች ከባህላቸው ለማፈንገጥ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

## 4. የጥናቱ ማብራሪያ

በዚሁ ክፍል የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች የሚተነተኑ ሲሆን ከዚሁ የጥናት ርዕስ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በሌሎች ጥናቶች ላይ የተገኙ ቁልፍ የጥናት ግኝት ውጤቶች እንደየአስፈላጊነታቸው ጥናቱን በሚያጠናክር መልኩ ተዳሰዋል፡፡ ይህ ጥናት ሶስት ዋና ዋና ግኝቶችን አመላክቷል፡፡ የመጀመሪያው የጥናት ግኝት የሃይማኖት አባቶች/እናቶች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸው የግንዛቤ ተመሳሳይና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑንና የባህል አፈንጋጭነትንም በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በአኗኗር ዘይቤ፣ በተለያዩ የበዓላት ወይም የለቅሶ ክዋኔዎች፣ በአረማመድ፣ በአሰራር፣ በሰላምታ አሰጣት፣ በመገልገያ ቁሳቁሶች ሊገለጥ እንደሚችል በአጠቃላይ ከባህል ማፈንገጥ ማለት ከተለመደው የአኗኗር፣ የአመጋገብና የአለባበስ ስርዓት ወጣ በማለት እንደሆነ አመላክቷል፡፡ ሁለተኛው ግኝት በሶስቱም የጥናቱ ተሳታፊ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ስለባህል አፈንጋጭነት ያልተሟላና ወደ አንድ ጎን ያጋደለ ግንዛቤ እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሶስቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች በተደረገ ንጽጽር መሰረት በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ከባህል አፈንጋጭነት ግንዛቤ አንፃር ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለ ያሳያል፡፡

ሶስተኛው ግኝት መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ከባህላቸው የሚያፈነግጡበት መንስኤ የአስተዳደግ ችግር፣ የአቻ ግፊት፣ የነበረው ባህል ጎጂ ሆኖ ሲያገኙት፣ የማህበራዊ ሚዲያ እና የመገናኛ ብዙሀን ተፅዕኖ የሚሉት ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጥናት ካካሄዱ ሙሁራን መካከል Irani (2008) የቤተሰብ ቁጥጥር ማነስ፣ የባህል ግትርነት፣ ተቀባይነት የሌለው ማህበራዊ ህግ እንዲሁም የባህል ወረራ ለፍንገጣ ዋና ዋና መንስኤዎች መሆናቸውን ገለፃል። Jaonan (2012) ለተማሪዎች የአፈንጋጭነት መንስኤዎች ከወላጆች ይልቅ አስተማሪዎች በተማሪዎች ላይ የሚሳድሩት ተጽዕኖ እንደሆነ ባካሄደው ስታስቲካዊ ፍተሻ አሳይቷል። Hossain (2014) የአፈንጋጭነት መንስኤዎች በጣም በርካታ እንደሆኑ ገልጾ እነዚህም እራሳቸውን የቻሉ ውስጣዊና ውጫዊ መሰረቶች እንዳሏቸው ያብራራል። አክሎም እነዚህ ምክንያቶች በጊዜ፣ በቦታ እና በተለያዩ ሁኔታዎች ሊለያዩ እንደሚችል በጥልቀት አስረድቷል። Poole (1989) አስተዳደግ ከሁሉም ለየት ያለ ቁልፍ ሚና እንደሚጫዎት እና ለተስተካከለም ሆነ ለተበላሹ የወጣቶች ባህርይ መገለጫዎች የቤተሰብ አስተዳደግ ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል ሲል ያጠናክራል። ይህ የሆነበት ምክንያት ቤተሰብ እንደ አንድ ትልቅ ማህበራዊ ተቋም ከሌሎች ዋና ዋና ተቋማት፣ ማለትም ከእምነትና ከትምህርት ተቋማት የበለጠ ተፅዕኖ ስላለው ነው ሲል ያብራራል። Selam (2011) የአፈንጋጭነት መንስኤዎች በአስተማሪዎች ላይ የሚስተዋለው የስነ-ምግባር ችግር፣ የትምህርት ቤቱ ህግና ደንብ በአግባቡ ያለመተግበር፣ ትምህርት ቤቱ ያለበት የተጋለጠ አቀማመጥ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እንደሆኑ ትገልፃለች። Conger (1991) ለአፈንጋጭነት እንደ ዋና መንስኤ ከሚጠቀሱ ነገሮች መካከል የአቻ ግፊት ግምባር ቀደም ተጠቃሽ ሊሆን እንደሚችል ያረጋግጣል።

ሌላው በዚህ ጥናት ከተገኙ ውጤቶች ውስጥ ለባህል አፈንጋጭነት እንደ ዋና መንስኤ ተደርጎ በጥናቱ ተሳታፊዎች የተጠቀሰው የማህበራዊ ሚዲያና የመገናኛ ብዙሀን ተጽዕኖ ነው። ከዚሁ ጋር በተገናኘ የተለያዩ የዘርፉ ተመራማሪዎች ስለጉዳዩ ወሳኝነት የራሳቸውን አሻራ አስቀምጠዋል። ለአብነት ለመውሰድ ያህል መሳፍንት (2009) እንደሚያብራራው ከሆነ በፍጥነት በሚለዋወጥ አለም ውስጥ ማህበራዊ ሚዲያና መገናኛ ብዙሀን ቀዳሚው የመረጃ ምንጭ በመሆን በሰዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ሁለንተናዊ የለት ከእለት ህይወት ውስጥ ከባድ ተፅዕኖውን እያሳረፉ ይገኛሉ። አሁን ባለንበት የሉዕላዊለት አለም ውስጥ የቴሌቪዥን ፕሮጋራሞች እና የተለያዩ ፊልሞች ለወጣቶች እና ህጻናት ቀዳሚ

የመዝናኛ ምንጭ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ በዚህም ምክንያት እነዚህ የቴሌቪዥን አውታሮች እና ፊልሞች የሚያሳዩት ትይንት እና ነውጠኛ መልእክቶች (violence) ለወጣቶች የባህርይ መበላሸት እና የባህል አፈንጋጭነት ዋነኛ መንስኤ እንደሆኑ ያስረዳል፡፡

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞ የተነሳው ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለአፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ እና የፍንገጣ መንስኤ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡- እነሱም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መግለፅ፣ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማሳየት እና መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ለምን ከባህላቸው ያፈነግጣሉ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ለመመለስ ደግሞ መረጃዎች ከ32 መምህራን፣ ከ34 ተማሪዎችና ከ31 የሃይማኖት አባቶች ከቀዳማይና ከካላዓይ የመረጃ ምንጭ በፅሁፍ መጠይቅ ቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ዓላማ መምህራን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት ነበር፡፡ በዚህም እነዚህ የህብረሰተብ ክፍሎች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ተመሳሳይና ዝቅተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም 23 (74.2%) የሚሆኑት የሃይማኖት አባቶች/እናቶች፣19 (59.4%) ያህል መምህራን እና 23 (67.6%) ተማሪዎች ስለባህል አፈንጋጭነት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁለተኛውን የጥናት ዓላማ ማለትም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል አፈንጋጭነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር ሲሆን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በተመሳሳይ የግንዛቤ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ የግንዛቤ ልዩነት እንደሌላቸው (P>0.05) የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡

በመጨረሻም መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ከባህላቸው የሚያፈነግጡበትን መንስኤ በተመለከተ በተለይም ለሃይማኖት አባቶችና ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ አስተዳደግ፣ የአቻ ግፊት፣ የነበረውን ባህል ጎጅ ሆኖ ሲያገኙት፣ የማህበራዊ ሚዲያ እና የመገናኛ በዙሀን ተፅዕኖ የሚሉት ምክንያቶች ዋነኛዎቹ እንደሆኑ ታውቋል፡፡

## 5.2. ይሁንታ

ከዚህ በመቀጠልም በጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ወደፊት በጉዳዩ ዙሪያ ሌላ ሰፋ ያለ ጥናት ማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች ምክንያታዊ የሆነ የይሁንታ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

- ከመምህራን ከተማሪዎችና ከሀይማኖት አባቶች መካከል በአንፃራዊነት የሀይማኖት አባቶች ስለባህል አፈንጋጭነት ምንነት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ለሃይማኖት አባቶች/እናቶች ስለአፈንጋጭነት ምንነት በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ቢሰጥ፣
- በመገናኛ ብዙሀን የሚቀርቡ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ከዜጎች ባህል፣ ሀይማኖት፣ ሥርዓት፣ ወግና ልማድ አንፃር እየተፈተሹ ወይም እየተመረመሩ ቢቀርቡ፣
- የተለያዩ ተመራማሪዎች የአፈንጋጭነት ምንነት በተመለከተ በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ተጨማሪ ጥናት ቢያካሂዱ
- በመጨረሻም ወላጆች የልጆቻቸው አስተዳደግ ሥነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ እንዲሆን በተቻላቸው መጠን ቢጥሩና የጓደኞቻቸውን ባህሪ በየጊዜው ክትትል ቢያደርጉ፡፡

## ዋቢ መፃህፍት


Alemayehu Tegenu Mekuria. 2012. Assessment of Students Misbehavior and Coping Strategies: In the Case of Shashemene Secondary School.

Conger, J. J. (1991). Adolescence and Youth: Psychological Development in Changing World. Fourth edition. New York City: Harper Collins Publisher.

Cohen, Louis; Manion, Lawrence, andMorrison, Keith (2000) *Research Methods in Education (5th ed.).* London and New York: RoutledgeFalmer.

Davis, R. (1970) *Teaching Reading Skills.* New York: MacMillan Publishing Company.

Dornyei, Zoltan (2007) *Research Methods in Applied Linguistics.Qualitative, Quantitative & Mixed Methodologies*. UK: OUP.

Dornyei, Zoltan and Taguchi, Tatsuya (2010) *Questionaries in Second Language Research Construction, Administration and Processing (2nd ed.).* New York and London: Routledge.

Downes, William (1984) *Language and Society.* London: Fontana Paper bates.

Emmanuel O.Ojameruaye (n.d) "Culture and Economic Development in Urhoboland" Retrieved from:http://www.waado.org/geography/development/ojameruaye_ culture_development1.htm

Fasold, Ralph (1984) *The Socio-Linguistics of Society.* London: Blackwell.

Field, A. (2009). Discovering statistics using SPSS (3rd ed.)SAGE Publications Ltd.

Hossain, Zahangir. 2014. Deviant Behavior: A Study of Causes, NU Journal of Humanities, Social Sciences & Business Studies Vol. 1, No. 1

Irani, Cyrus (sep.23, 2008) "Exploring Causes of Social Deviation."Retrieved from:www.helium.com/items/1191010-exploring-causes-of-social-deviation on 15/08/05.

Jourdan, Christine & Tuite, Kevin (2006) "Language, Culture, and Society: Studiesin the social and cultural foundations of Language." USA: CUP.

Liddicoat, Anthony J. (2011) "Language Teaching and learning from an Inter cultural Perspective." In Hinkel,Eli (ed.) *Hand Book of Research in Second Language Teaching & Learning Vol. II (pp.542).* NewYork &London: Routledge.

Long, Russ (2012) "Introduction Sociology: Deviance" Retrieved from: http://dmc122011.delmar.edu/socsci/rlong/intro/deviance.htm

Lyons, John (1981) *Language and Linguistics*. London: Cup.

May, F.B. (1990) *Reading as Communication an Interactive Approach (3rded.)*. USA: Me rill Publishing Company.

Mesafint Adal. (2009). Juvenile Delinquency and Its Treatment: A Study on Addis Ababa Juvenile Delinquents Rehabilitation Institute. MA Thesis, Department of Sociology, Addis Ababa University. Addis Ababa.

Nieto, S.(ed.) (2010) *Language, Culture, and Teaching: Critical Perspectives*. New York & London: Rutledge.

Oha, Anthony C. et al. (2010) "Introduction to Socio-Linguistics." Abuja: National Open University of Nigeria. Retrieved from: www. non.edu.ng/noun/ NOUN-OCL/ pdf/pdf2/ ENG355. pdf

Poole, E. M. (1989). Adolescent in Transition: A Life-course Perspective. In

Hurrelmann, K. and Engel, U. (Ed.), The Social World of Adolescents: International Perspective. Berlin: Walter de Gruyter.

Salinger, L. M. (Ed.). (1998). Deviant Behavior 98/99.3rd edition. Guilford,

Connecticut: Dushkin/McGraw-Hill

Selam Esayas. 2011. The School and Deviant Behavior: A Case Study of

Youth in BoleSecondary High School and Dandi Boru School in Addis Ababa, A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for theDegree of Master ofArts in Sociology